ቀይ ቀበሮን ካናይን ዲስቴምፐር በሽታ እንከላከል!

ቀይ ቀበሮዎች ከዓለም በኢትዮጵያ ከፍተኛ ደጋማ አካባቢዎች ብቻ የሚገኙ አጥቢ ብርቅየ የዱር እንስሳት ሲሆኑ ቁጥራቸውም 500 አይበልጥም። በሀገራቱ የተለያዩ ከፍተኛ ቦታዎች ከባህር ወለል ከ3000 ሜትር በላይ ይገኛሉ። በኦሮሚያ በባሌና በአርሲ፣ በአማራ በሰሜን ተራራዎችና በቦረና ሳይንት ብሔራዊ ፓርኮች እንዲሁም በመንዝ ንሳ፣ አቡነ ዩሴፍና አቦይጋራ እና ደላንታ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራዎች የሚገኙ ሲሆን የሚኖሩትም በቡድን ነው።



ቀይ ቀበሮዎች በተለያዩ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች ለጉዳት ይዳረጋሉ።

በሀገራችን በከፍተኛ ደጋማው አካባቢ የሚኖረው ህዝብ ብዛት በከፍተኛ ደረጃ በመጨመሩ የተነሳ የስርዓተ ምህዳሩና ብዝሃ-ህይወት ሀብቱም በከፍተኛ ደረጃ እየተራቆተና እየተመናመነ ይገኛል።

በዚህ የተነሳ፡-

1. የእርሻ ስራና ልቅ ግጦሽ እየተስፋፋ በመምጣቱ የተነሳ የቀይ ቀበሮ መኖሪያ ቦታ ከማጣበቡም ባሻገር ቀይ ቀበሮዎች ለምግብም እጥረት ተዳርገዋል።

2. ውሻዎች በቀጥታ ወደ ቀይ ቀበሮዎች የመኖሪያ አካባቢ በመግባት የተለያዩ በሽታዎችን ከማስተላልፍም ባሻገር የመዳቀል ችግርንም ያስከትላሉ።

ቀይ ቀበሮዎችን ከሚያጠቁ በሽታዎች ውስጥም ውሻን የሚያሳብድ በሽታና ካናይን ዲስቴምፐር በዋናነት ይጠቀሳሉ።

ካናይን ዲስቴምፐር /ሃርድፓድ/ ምን አይነት በሽታ ነው?

ይህ በሽታ ሀይለኛና አጣዳፊ ተላላፊ የሆነ በርካታ የውሻ ዝርያ ያላቸውንና ሌሎችን የቤትና የዱር እንስሳትን ዝርያዎች የሚያጠቃ የበሽታው አምጪ ህዋሱም ካናይን ዲስቴምፐር ቫይረስ /Canine Distemper Virus/ ይባላል።

በሽታው ሁሉንም የእንስሳቱን የአካል ክፍሎች የሚያጠቃ ቢሆንም በዋናነት የስርዓተ-ነርቭ፣ የምግብ ስርዓተ እንሽርሽሪት፣አይን፣ የመተንፈሻ አካል በተለይ ሳምባና ሌሎች የእንስሳቱ አካል በተለያየ ደረጃ ያጠቃል።

በበሽታው የሚጠቁ ዝርያዎች

ለማዳ ውሻዎች፣ ተራና ቀይ ቀበሮዎች፣ ጅብ፣ ሽለመጥማጥና የድመት ዝርያ የሆኑት አንበሳ፣ ነብርና አቦ ሸማኔ የመሳሰሉት የዱር እንስሳት በተለያየ ደረጃ በበሽታው ይጠቃሉ። አልፎ አልፎ ቢሆንም ዝንጀሮና የእስያ ዝሆን በበሽታው የሚጠቁ መሆኑን ጥናቶች ያስረዳሉ።

በተለይ በለጋ እድሜ፣ በዝቅተኛ የጤንነት፣ የአመጋገብና አኗኗር የሚገኙ እንስሳት በይበልጥ በዚህ በሽታ ይጠቃሉ። ከዚህም ውስጥም በዋናነት ቀይ ቀበሮዎች ይጠቀሳሉ።

የበሽታው ምልክት

በሽታው ለማዳ ውሻዎች፣ ቀይ ቀበሮዎችንና ሌሎችን የዱር እንስሳት የሚያጠቃ ሲሆን በተለይ ቡችሎችን እስከ 4 ወር እድሜ ክልል የሚገኙት በከፍተኛ ደረጃ ያጠቃል።




ስዕል 1. መጀመሪያ ውሃ መሰል ወፈር ያለና የሚያጣብቅ ፈሳሽ ከአይን መታየት

በመጀመሪያ ከ3 እስከ 6 ቀናት የሚቆይ ትኩሳትና ውሃ የሚመሰል እንባ በኋላም የሚያጣብቅና ወፈር ያለ መግል መሰል ፈሳሽ ከታመሙ እንስሳት ዓይን ይፈሳል፡፡ በመቀጠልም ሳል፣ ንፍጥና የምግብ ፍላጎት መቀነስ በተጨማሪም ትኩሳት ለሁለተኛ ጊዜ ይታያል፡፡

ጎላ ብለው የሚታዩ የበሽታው ምልክቶችም ትኩሳት፣ ሳል፣ ተቅማጥና ተውኪያ፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስና ማቆም፣ የሰውነት ፈሳሽ መቀነስና ቫይረሱ በተጨማሪም ስርዓተ ነርቮችን በመጉዳቱ የተነሳ የሰውነት ሚዛን መሳት፣ ማቀጥቀጥ፣ አንገት መድፋት፣ በከፊል /መሉ በሙሉ/ የጡንቻ መዛል፣ እራሱን ወደ አንድ በኩል ማዘንበልና ማዞር፣ ለማየት መቸገርና አንዳንድ ጊዜም በፍጥነት የሚሞቱበት ሁኔታ ይታያል፡፡ በሽታው እየበረታ ሲሄድ ትውኪያ፣ ቅዘንና የሳምባ ህመምና ድካም የተነሳ ይሞታሉ፡፡

አንዳንድ እንስሳት በሽታውን ተቋቁመው በሚያገግሙበት ጊዜ የእግር መዳፍ ማበጥ፣ የአፍንጫ እብጠትና መግል የያዘ የቆዳ ላይ ቁስል ይታያል፡፡



ስዕል 2፡.በአፍንጫና ግንጭል ላይ እብጠጥትና ቁስል



የስዕል 3 .የእግር መዳፍና ጣት ማበጥ

የበሽታው መተላለፊያ መንገዶች

በአብዛኛው ቡችላዎችና ውሻዎች በአየር ወለድ በሽታ አይነት የሚጠቁ በመሆኑ ቫይረሱ በአየር አማካኝነት ወደ ሳምባ ከታመሙ እንስሳት ጋር በቅርብ በሚደረግ ግንኙነት በሽታው ወደ ጤነኛ እንስሳት በቀላሉ ይተላለፋል፡፡

በሌላ በኩል ከታመሙ እንስሳት የሚወጡ ፈሳሾች ማለትም ቅዘን፣ ትውኪያ፣ልሃጭ፣ ኩስና ሽንት የተበከለ ምግብ መብላትና ውሃ በመጠጣት በበሽታው ሊያዙ ይችላሉ፡፡

ምርመራ

በሽታው ከሚያሳያቸው ምልክቶችና ከሚጠቁ እንስሳት ዝርያዎች ፣የእድሜ ደረጃ አኳያ መጠርጠርና መገመት ቢቻልም አስተማማኝ ዘዴ ግን ከታመሙ ወይም ከሞቱ እንስሳት አካል ተገቢውን ናሙና በባለሙያ በመሰብሰብና በላብራቶሪ በሚደረግ ምርመራ የበሽታው መንስኤ ማወቅና ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ህክምና

በሽታው በቫይረስ የሚመጣ ስለሆነ ቀጥተኛ የሆነ ፈዋሽ መድሃኒት የለውም፡፡ ነገር ግን ደጋፊና የነፍስ አድን ህክምና ለለማዳ እንሳስት በመስጠት ከበሽታው እንዲያገግሙ ይደረጋል፡፡

የበሽታው መከላከያ ዘዴዎች

ከእንስሳት ወደ እንስሳት በሽታው የሚተላለፍበትን መንገድ በማጤን መከላከል ይቻላል፡-

- በበሽታው የታመሙ እንስሳትን ከቦታ ቦታ እንዳይዘዋወሩ በመቆጣጠር ከጤነኛ እንስሳት ጋር ግንኙነት እንዳይኖር በማድረግ የበሽታውን የመዛመት እድል መቀነስ፣
- ለታመሙ እንስሳት ለይቶ ተገቢውን ነፍስ አድን ንጥረ-ነገርና ፈዋሽ መድሃኒት መስጠት፣
- ከታመሙ እንስሳት የሚወጡ ፈሳሾችን በተገቢው መንገድ ማስወገድ፣
- የውሻዎችን እንቅስቃሴ በመቆጣጠር ከቀይ ቀበሮዎች ጋር ግንኙነት እንዳይኖር ማድረግ፣
- ህብረተሰቡ ስለበሽታው በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ስልጠና በመስጠት በሽታውን መከላከል እና እንደአስፈላጊነቱ ለቀይ ቀበሮዎችና ለውሻዎች የመከላከያ ክትባት መስጠት በተጨማሪም በቤት ወይም በዱር እንስሳት የበሽታው ምልክት ሲታይ በቅርብ ለሚገኘው የእንስሳት ህክምና ክሊኒክ ወይም የጥብቅ ስፍራ ጽ/ቤት ወዲያውኑ በማሳወቅ በቅንጅት መከላከል ይቻላል፡፡

በአብክመ የአካባቢና ደን ጥበቃ ባለስልጣን
የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ዳይሬክቶሬት
ፖ.ሣ.ቁ.695
ስልክ፡+251 583208405
ዋና አዘጋጅ ፡ አለማየሁ ቢተዋ(251918288838)
የዱር እንስሳት ህኪም
አርታዒ፡ የስራ ክፍሉ ባለሙያዎች
ታህሳስ 2017 ባህር ዳር